**ራዕይ**

በ2022 ዓ/ም አዲስ አበባ ፅዱ፣ የደረቅ ቆሻሻ ዑደታዊ ምጣኔ ሀብትን ተግባራዊ ያደረገች የአፍሪካ ሞዴል ከተማ ሆና ማየት፡፡

**ተልዕኮ**

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን ግንዛቤ በማሳደግና በማሳተፍ፣ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጡን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ እና ዑደታዊ ምጣኔ ሀብትን ስራ ላይ በማዋል ከተማዋን ፅዱ ማድረግ ነው፡፡

**እሴቶች**

- ፍትሀዊነት
- ተጠያቂነት
- አገልጋይነት
- የስራ ላይ ደህንነት
- ደረቅ ቆሻሻ ሀብት ነው
- ፅዱና ዘመናዊነት

**የተቋሙ ዓላማ ፈጻሚ ዳይሬክቶሬቶች ዋና ዋና ተግባራት**

**1. የግንዛቤ፣ ህብረተሰብ ተሳትፎና የአካበቢ ንፅህና አጠባበቅ ዳይሬክቶሬት**

- በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ላይ ለነዋሪው ህብረተሰብ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ነዋሪውን ህብረተሰብ በንቃት በማሳተፍ የአካበቢ ንፅህና ማስጠበቅ

**2. የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎትና ግብዓት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት**

- የመንገድና የመንገድ ዳርቻዎችን ጽዳት መጠበቅ
- ደረቅ ቆሻሻን የመሰብሰብና ማጓጓዝ አገልግሎት መስጠት
- የደረቅ ቆሻሻ ፋሲሊቲዎችና ግብዓቶችን ማስተዳደር
- የፊሊት ማኔጅመንት ቴክኖሎጅን መተግበር፤
- የክፍያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ማረጋገጥ አገልግሎት

**3. የመልሶ መጠቀምና ዑደት ማድረግ ዳይሬክቶሬት**

- ደረቅ ቆሻሻ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ
- በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ የገበያ ትስስር መፍጠር

**4. የላንድፊል አስተዳደርና ብክለት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት**

- ደረቅ ቆሻሻን የማስወገድ አገልግሎት መስጠት
- ከላንድፊል የሚመነጭ ብክለትን መቆጣጠር፤
- የላንድፊል ማሽነሪዎች ክብካቤና ጥገና ማድረግ
- የረጲ ላንድፊልን የአገልግሎት ጊዜ/ዕድሜ ማራዘም

**5. የጥናትና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት**

- የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ማሻሻያ ጥናቶችን ማከናወን

- ፕሮጀክቶችን መቅረጽና መተግበር
- በደረቅ ቆሻሻ ዙሪያ የቀረቡ ፕሮፖዛሎችን መገምገምና የስራ ፍቃድ መስጠት
- ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት

በአዲስ አበባ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ስድስት አስርተ አመታት በላይ እየተከናወነ የመጣ ተግባር ነው፡፡ ይህም የቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና የአወጋገድ ስራ በማዘጋጃቤታዊ ዘርፍ ሲተገበር የቆየ ቢሆንም ከስራዉ ውስብስብና አስቸጋሪነት ጋር ተያይዞ በተለያየ የተጠሪነት እርከን ሲከናወን መቆየቱን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በከተማዋ ደረቅ ቆሻሻን መሰብሰብ፣ ማጓጓዝና ማስወገድ የተጀመረው ከ1901ዓ.ም ጀምሮ ማዘጋጃ ቤታዊ ተቋም ውስጥ የከተማዋን ጽዳት በመከታተል እስከ 1985 ዓ.ም ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከ1986 እስከ 1994 ዓ.ም በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ስር በንጽህና እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መምሪያ፣ከ1995ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ጽዳት ውበት እና መናፈሻ ልማት ኤጀንሲ፡፡

ከሐምሌ 2001 ዓ.ም እስከ 2010 ዓ.ም በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስር "የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ እና የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ማስወገድ ፕሮጀክት" የሚለዉን ስያሜ በመያዝ ሲሰራበት ቆየ፡፡ ከ2010 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ደግሞ "የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ" በሚል ስያሜ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ" የሚለውን ስያሜ በማግኘት የከተማዋን ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ፣ የሚጠቅመውን ቆሻሻ ወደ መልሶ መጠቀም በመለወጥና የማይጠቅመውን የማስወገድ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 74/2014 የተቋቋመው ኤጀንሲው፤በስሩ የጥናትና ፕሮጀክት ትግበራ ዳይሬክቶሬት፣ የመልሶ መጠቀምና ዑደት ማዕከላት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት፣የግንዛቤና ስርፀት የህብረተሰብ ተሳትፎ ዳይሬክቶሬት እና የላንድ ፊል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመባል በአምስት ዋና ዋና ዳይሬክቶሬት ተደራጅቶ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡